# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 77 ጥቅምት 26 2002 ዓ.ም ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ይህ ነው የወያኔ እውነተኛ ታሪክ። ቆምኩለት የሚለው ሕዝብ ሲራብ የሚፈነጥዝ፤ የእርዳታ እህልን እየነጠቀ የከበረ "ነፃ አውጪ"። በእርዳታ ገንዘብ ጉና የንግድ ድርጅትን አቋቁሞ፤ ኤፈርትንና ደጀናን አደራጅቶ በስታሊናዊው ማሌሊት . . . ዝርዝሩን ገጽ 3 ያንቡ

## የመለስ በህክምና ወደ በልጅዬም መመላለስ ዜና መውጣት ሁለት የኤምባሲ ሠራተኞችን ከሥራ አፈናቀለ

ለመለስ ዜናዊ ባለው ልዩ ቅርበትና ታማኛነት ላለፉት 18 አመታት በመጀመሪያ በአሜሪካን አገር ቀጥሎ ደግሞ በአውሮጳ ህብረት የወያኔ አምባሳደር ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኘው ብርሀኔ ገብረክርስቶስ፣ የአለቃውን በከፍተኛ ህመም ምክንያት ወደ ቤልጅዬም መመላለስ ለግንቦት 7 ድምጽ መረጃ አሳልፈው ሰጥተዋል በማለት የጠረጠራቸውን ሁለት በኤምባሲው ተቀጥረው ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሰራተኞችን ከሥራቸው እንዳፈናቀለ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከሥፍራው መዘገቡን የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ባለፈው ማክሰኞ ጥቅምት 24 ቀን ስርጭቱ አስደምጦአል ። በአምባሳደሩ ቤት ዋና ምግብ አዘጋጅ የነበረቺው ፊሊፕናዊ ዜጋ ወ/ሮ ማሪያ ታዛንጎና ገነት ጥላሁን የተባለች የባህል ምግብ አዘጋጅ ከስራቸው ለመፈናቀል የበቁት የግንቦት 7 ድምጽ የመለስ ዜናዊን በሚስጥር ወደ ቤልጅዬም መመላለስ ዜና በመዘገቡ እንደሆነና "ከእናንተ ሌላ የርሱን ለህክምና ወደዚህ አገር መምጣት የሚያውቅ የለም" የሚል ውንጀላ በብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ ከተሰነዘረባቸው ቦኋላ መሆኑን ሁለቱም የጥቃቱ ሰለባዎች ለቃለ መጠይቅ ፈልጎ ላገኛቸው የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ በሰጡት መግለጫ አረጋግጠዋል ።

የሰራተኞቹ ከአምባሳደሩ ቤት መባረር ለግንቦት 7 መረጃ ክፍል ጥቆማ እንደ ደረሰ ወዲያውኑ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ተባራሪ ግለሰቦቹን አፈላልጎ በማግኘት አጭር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የቻለ ሲሆን፣ ከቃለ ምልልሱ ለመረዳት እንደተቻለው ብርሀኔ ገብረክርስቶስ በተደጋጋሚ በሚወጣው ዜና እጅግ እንደተረበሸ ለማወቅ ተችሎአል። አምባሳደር ተብየው በተደጋጋሚ " የመለስን መምጣት ከእናንተ በስተቀር ሌላ ሊያውቅ የሚችል ሰው የለም፣ መረጃውንም የምታወጡት እናንተ ናችሁ፣ ይህን ባታወጡ አስግረፋችሁዋለው" እያለ በሰራተኞቹ ላይ ይዝት እንደነበር በተለይም በኢትዮጵያዊቷ ገነት ጥላሁን ላይ ዛቻና ማስፈራራቱ ያይል ስለነበር ወደ አገር ቤት ከተመለሰች የተዛተባት እስራትና ድብደባ እንደማይቀርላት በመፍራት ከቤቱ ወጥታ ተደብቃ እንደምትገኝ ለቅሶ በተቀላቀለብት ስሜት ገልጻለች ።

ወ/ት ገነት ላለፉት ስድስት አመታት በብርሀኔ ገብረክርስቶስ ቤት ትሰራ እንደነበር የገለጸች ሲሆን፣ በሁለቱ መካከል የነበረው ግንኙነት **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ምርጫ 2002ን ተከትሎ ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስ እንደሚችል ከፖሊስ የወጣው መረጃ አጋለጠ። ወያኔ የአድማ መበተኛ መሳሪያ ግዥ ላይ ተጠምዶአል

ወያኔ ፋሽስታዊ አገዛዝ ዕድሜውን ለሌላ 5 ዓመት ለማራዘም የሚያደርገውን የዘንድሮ ምርጫ ተከትሎ ሊነሳ ይችላል ተብሎ የሚያሰጋውን አመጽ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የአድማ መበተኛ መሳሪያ ጊዥ ጫረታ ማውጣቱ ታወቀ ፣ ይህም ምርጫ 2002ን ተከትሎ ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቀስ ይችላል የሚል ስጋት በወያኔ ዘንድ መኖሩን የሚያመለክት ነው ተብሎአል።

ከፌደራል ፖሊሲ ኮሚሽን የውስጥ ምንጮቻችን ሰሞኑን በደረሰን መረጃ መሰረት ፣ እነዚህ የግዥ ጫረታ የወጣባቸው የአድማ መበተኛ መሳሪያዎች ዝርዝር ፡ በሰለጠነው ዓለም ጭምር ለተመሳሳይ አላማ ሥራ ላይ ከሚውሉ የመሳሪያ ዓይነቶች ተርታ የሚመደቡ በመሆናቸው፡ ወያኔ በሥልጣኑ የሚመጣበትን ማንኛውንም ዓይነት ስጋት ለመጨፍለቅ በእጁ የሚገኘውን የመግደያ መሳሪያ ከመጠቀም የማይታቀብ ሃይል መሆኑን በድህረ ምርጫ 97 ከወሰደው ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ላስተዋለ ምናልባት ይህ አዲሱ ጥረት የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ መሰረቱ የሆነውን የምዕራቡን አለም ለማታለል እንደሆነ ከመረጃው ጋር ተያይዞ ከተላከልን አስተያየት ለማወቅ ተችሎአል ።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ባደረገው ማጣራት፡ እነዚህ የመሳሪያ ግዥ ጨረታ ዝርዝር ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ ለሆነው ታላላቅ የዲፕሎማቲክ ሚሽኖች በሙሉ እንዲደርሳቸው የተደረገ በመሆኑ ፡ ወያኔ በመጭዊ ምርጫ ተብየው ተውኔት አሸናፊ ሆኖ እንደሚወጣ ከወዲሁ ለማረጋገጥ በመቻሉ ምናልባትም ሊነሱ ይችላሉ ተብለው የሚጠበቁ አነስተኛ ውዝግቦች ከተከሰቱ በሰለጠነና በሰው ህይወት ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ሊቀንስ በሚችል ሃላፊነት በተሞላበት አሰራር ለመፍታት ፈቃደኝነት ያለው መስሎ ለመታየት እንደሆነ ለደህንነት ጉዳይ ስማቸውን መግለጽ የማይቻል መረጃውን ያቀበሉን የፖሊስ ኮሚሽን ባልደረባ ለዘጋቢያችን ከሰጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሎአል ።

ግዜ

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በተሰጠ ቀጥተኛ የግድያ ትእዛዝ ያለቁ የዲሞክራሲ ሰማእታት በመታሰብ ላይ ናቸው

በግንቦት 1997 አም የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ የመለስ ዜናዊ ዘረኛና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ያደረገውን ዘረፋ በመቃወም አደባባይ የወጡና በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትእዛዝ በጥቅምት ወር የተገደሉት የዲሞክራሲ ሰምአታት አራተኛ አመት በመታሰብ ላይ ነው።

መለስ ዜናዊ የፈጸመው ጭፍጨፋ ጣሊያናዊው ግራዚአኒ በየካቲት 11፣ 1928 አም በአዲስ አባባ ከተማ በንጹህ ኢትዮጵያውያን ላይ ከፈጸመው ጭፍጫ ቀጥሎ፣ በጠራራ ጸሀይ የተፈጸመ ሁለተኛው ከባድ ጭፍጫ ሲሆን፣ የአምባገነኑ አገዛዝ ግን እስካሁን ድረስ ሃላፊነቱን አልወሰደም። የመለስ ዜናዊ ለፍርድ አለመቅረብ በርካቶችን እያንገበገበ የሚገኝ ጉዳይ ቢሆንም፣ አገራችን ከአምባገነነኖች አገዛዝ ነጻ ስትወጣ፣ ግለሰቡን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስቸሉ በርካታ መረጃዎች ተሰባስበው መቀመጣቸው ይታወቃል።

መለስ ዜናዊ ህጻናቱን ፈጅቶ በሰላም እስከዛሬ ድረስ መቆየቱ ያንገበገባቸው፣ ሁለት ልጆቻቸውን በአጋዚ ጥይቶች የተነጠቁ እናት ሲናገሩ "የልጆቻችን ደም ዛሬ አስታዋሽ ያጣ ቢመስልም፣ አንድ ቀን በክብር በየአመቱ እንደሚዘከሩ እናምናለን፣ ያን ጊዜ ልጆቻችን የተሰውለት አላማም ግቡን ይመታል፣ የልጆቻችንም ነፍስ በሰላም ታርፋለች" ብለዋል። እኝህ እናት አክለውም "ሁለቱ ልጆቼ ዛሬ በህይወት የሉም። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በአባላቱ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ምስክርነት አሰማ

የደቡብ ጎንደር ነዋሪ የሆነች አንዲት የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ አባል ከእስር እና ከእንግልት በተጨማሪ የአስገድዶ መደፈር ወንጀል እንደተፈጸመባት አዲስ አድማስ የተባለው ጋዜጣ ዘገበ።

"የዜጎች ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች መረገጥ ይቁም"በሚል ርእስ ባለፈው አርብ አንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ባካሄደው ስብሰባ በወያኔ አሰቃቂ ግፍ የተፈጸመባቸው አባላቱ የደረሰባቸውን መከራ; የተቃዋሚ አመራሮች፤የምእራብ ሀገራት ዲፕሎማቶች እና ጋዜጠኞች በተገኙበት በዚህ መድረክ ምስክርነታቸውን መስጠታቸው ታውቋል።

የደብብ ጎንደር ነዋሪ የሆነች የአንድነት አባል ከሶስት ወር በፊት በወያኔ ከመታሰሩዋም በላይ ተገዳ እንደተደፈረች ገልጻለች።ሴቶችን አስገድዶ መድፈር እና ማጥቃት በፋሺስቱ የወያኔ ብድን ዘንድ እንደ ጀቡዱ እና በህብረተሰቡ ላይ የፓለቲካ ሽብር ማንገሻ ተደርጎ እንደሚቆጠር በአጋዴን እህቶቻችን ላይ የደረሰው ጉልህ አብነት ነው ተብሎአል።

ተገዳ ከተደፈረችው የአንድነት አባል በተጨማሪ ከጋሞ ጎፋ ዞን ሰላም ከተባለ AKABABI የመጡ የአንድነት አባል ካለ ምንም ጥፋታቸው ባለፈው አመት ሁለት ጊዜ ከመታሰራቸውም በተጨማሪ ንግዳቸው ታግዶ ንብረታቸው መወረሱን ተናግረዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የወያኔ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በቅርቡ ከሶስት ፓርቲዎች ጋር የተደረገውን የይስሙላ የምርጫ ስነምግባር ስምምነት አስመልክቶ የሚያቀርቡት ዜና ህዝቡን በእጅጉ ማሰልቸቱ ታወቀ

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን የላከልን ዘገባ እንደሚያመለክተው ከሆነ፣ የወያኔ የዜና ማሰራጫዎች የይስሙላውን ስምምነት እንደትልቅ ድል በመቁጠር ጧትና ማታ እያቀረቡት ይገኛሉ። ይሁን እንጅ የህዝቡ ስሜት አሁንም ከ 1997ቱ ምርጫ ጋር መሆኑን የሚናረገው ዘጋቢያችን፣ በእየለቱ የሚደረገውን ቅስቀሳ የሚሰማ ሰው እንደሌለ ከተለያዩ አካባቢዎች ያሰባሰበውን መረጃ አጠናክሮ ዘግቧል።

በላፍቶ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የአንድ ሆቴል አስተዳዳሪ ሲናገሩ " ወያኔ ማለት የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ በመሆኑ ህዝቡ ከበጉ ለምድ አልፎ ተኩላውን ማየት ከጀመረ ከአምስት አመት በላይ ሆኖታል፣ አሁንም ያው ተኩላ በግ ነኝ እያለን ነው፤ እኛ ደግሞ አሁንም ተኩላ ነህ እያልነው ነው" ይላሉ። እኝሁ አስተያየት ሰጪ አክለውም ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ከእርሱ ጋር የሚደረግ ድርድር እርባና የለውም፣ ይልቅስ ዋናው ወያኔን ለማስወገድ ጠንካራ ትግል ማካሄድ ነው" ብለዋል።

ሌላ አስተያየት ሰጪ ደግሞ የወያኔን የወሬ ነጋሪዎችን ማዳመጥ ከአቆሙ አምስት አመት ማስቆጠራቸውን ተናግረው፣ በወያኔ ሬዲዮ እየተነገረ ያለውን ቅስቀሳ ባለመስማታቸው አስተያየት ለመስጠት እቸገራለሁ ሲሉ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# ችጋርና ወያኔ መንትያ ችግሮቻችን ናቸው፤ ሁለቱንም ለማስወገድ ቆርጠን እንነሳ!

ወያኔን በጥልቀት የሚያውቁ፤ መሥራችና ከፍተኛ የአመራር አባላት የነበሩ ሰዎች ዛሬ በተለያዩ መድረኮች ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው። በተለይም [1]አቶ ገብረመድህን አርአያ፣ አቶ አስገደ ገ/ስላሴ እና አቶ አረጋዊ በርሀ ስለ ቀድሞ ድርጅታቸው የሰጧቸው ምስክርነቶች በወያኔ ላይ የነበረንን አቋም ትክክለኝነትን ይጠራጠሩ ለነበሩ ወገኖቻችን ተጨባጭ ማስረጃዎች ሁነዋል ብለን እናምናለን።

አቶ ገብረመድህን አርአያ "የትግራይ በጠላት እጅ መውደቅና በኢትዮጵያ ያስከተለው መዘዝ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጽሁፍ

* የችጋርና የወያኔ መንትያነት አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ውስጥ የተፈጠረ ሳይሆን ከደደቢት፣ ወርዒ እና ደጀና ጀምሮ የመጣ መሆኑን፤
* ወያኔ የትግራይን ሕዝብና ረሃብን መጠቀሚያ አድርጎ እዚህ መድረሱን፤ እና
* ይህም በሃገራችን ኢትዮጵያ ላይ መዘዝ ማስከተሉን በዝርዝር ያብራራል።

የአቶ አረጋዊ "አጉል ሙገሳ ወይስ እውነተኛ ታሪክ?" የተሰኘው ጽሁፍም ይህንኑ ያጠናክራል። የአቶ አስገደ ገ/ስላሴ ቃለምልልስ ደግሞ የወያኔን መሰሪነት በተጨማሪ ማስረጃዎች ያረጋግጥልናል።

1977 ዓ.ም. ከ6.5 ሚሊዮን በላይ ወገኖቻችን የተራቡበትና ከዚህም ውስጥ ከሚሊዮን በላይ የሆኑት የሚደርስላቸው ጠፍቶ በረሃብ ያለቁበት ዓመት እንደሆነ በሃዘን የምናስታውሰው ነው። ይህ ዓመት ለነዚህ ወገኖቻችን የችጋርና ሰቆቃ ዓመት የነበረውን ያህል ለደርግና ወያኔ ግን የጥጋብና ፈንጠዚያ ዓመት ነበር። ደርግ አስረኛ ዓመት በዓልና የኢሠፓ ምስረታን ለማክበር አሁን የመለስ መንፈላሰሻ የሆነውን አዳራሽ አሠርቶ በድግስ ሲንበሻበሽ፤ ወያኔም በበኩሉ አሁን የምስጢር እስር ቤት ሆኗል ተብሎ የሚገመተውን የወርዒ አዳራሽን አሠርቶ በድግስ ተንበሽብሿል። ስለዚያኔው ደርግ ብዙ የተባለ ስለሆነ እዚህ ላይ ማንሳት አያስፈልግም። ስለ ወያኔው ድግስ ግን ከአቶ ገብረመድህን አርአያ ጽሁፍ ስለ ወርዒ አዳራሽ ከሰጡት ማብራሪያ በመጀመር በስፋት እንጠቅሳለን።

*ለአዳራሹ ሥራ በጠቅላላ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ብር የወጣ ሲሆን 500 እንግዶችን እንዲይዝ ተደርጎ የተሰራ ነው። አዳራሹ ጣሪያውና ግድግዳው በቀይ ጨርቅ ተሸፍኖ የማርክስ፣ የሌኒንና የስታሊን ምስሎች ብሎም ማጭድ፣ መዶሻና ኮከብ ያሉበት በብጫ ቀለም እና ብልጭ ድርግም በሚሉ መብራቶች በማሸብረቁ ለተመልካች በሌሊት የሰለጠነች ከተማ ይመስል ነበር። ......*

*ጉባኤው ሐምሌ 5 ቀን 1977 ዓ.ም. ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ሥራውን ጀመረ። የአዳራሹ ሁለት በሮች ተከፈቱ፤ በጣም አሸብራቂና ልዩ ነበር። የማናውቀው ገነት የገባን እንጂ በሰው እጅ የተሰራ አይመስልም። በጉባኤው ፊትለፊት በአማሪ መልክ የተሰራ ሙሉውን በቀይጨርቅ የተሸፈነ የኮሚኒስት አርማ ይታያል። ከቀኝ ወደ ግራ ማርክስ፣ ሌኒንና ስታሊን በትልቅ ፍሬም ሆነው ይታያሉ። የስብሰባው መሪዎች ትልቅ ጠረጴዛ በቀይ ጨርቅ ያጌጠ የህወሓት ባንዴራ አለው ......*

*ይህ ጉባኤ የተካሄደው የትግራይ ሕዝብ በድርቅ ምክያት እንደቅጠል እየረገፈ ባለበት ወቅት ነው። የጉባኤው ወጭም ከዚሁ ሕዝብ የተነጠቀ ሃብት ነው። የሰው ልጅ እየረገፈ በየመንገዱ ቀባሪ አጥቶ የጅብ ቀለብ በሆነበት ወቅት ነው ስብሰባው ለ15 ቀናት የተካሄደው። የጉባኤውን ቆይታ ወጭ ለትዝብት እንመልከት ..... የምግብ ዋና ኃላፊ ወ/ሮ ኤልሳ አስፍሃ የፃድቃን ገ/ጻዲቅ ሚስት ስትሆን በእሷ እዝ ስር በቅድመ ዝግጅቱ 300 ከብቶች ለእርድ ቀርበዋል። በቀኑ ከ7 እስከ 10 ከብቶችና 2 ፍየሎች ይታረዳሉ። ሁሉ ጉባኤተኛ የሚመገበው የነጭ ጤፍ እንጀራ ነው። በየቀኑ ጠዋት ቁርስ አምባሻና ሥጋ ጥብስ ሆኖ ምሳና እራት ቀይ የሥጋ ወጥ፣ ጥብስ ይቀርባል። በተጨማሪም የታሸጉ ፍራፍሬዎች እና አትክልት እንደ ልብ ነው። መጠጥ ጠጅ፣ የጠራ ጠላ እንደ ውሃ ይንቆረቆራል፤ እንደዚሁም ዊስኪና ቢራ በጅምላ ነው። የጉባኤው ተሳታዎች አብዛኛዎቹ የተገኙት ከነሚስቶቻቸው በመሆኑ ምርጥ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላ ከሱዳን ተገዝቶ እየተንፈላሰሱ ናቸው። በዚሁ መሠረት በቀን የሚወጣው ወጪ እንኳንስ ሽምቅ ተዋጊ ቀርቶ የአንድ ሃብታም ሃገር መንግሥትም ሊያወጣው የማይችል ነበር። ...*

*መስከረም 1978 ዓም ፓሊት ቢሮው ክሳድ ግመል በተባለ ቦታ ተሰብስቦ በድርቅ የተጎዳ ሕዝብ የተሰጠውን እርዳታ በግልጽ ለመዝረፍ ውሳኔ የሰጠበት ወቅት ነው። በውሳኔው መሠረት ከእርዳታ የሚሰበሰበው ንብረት በሚከተለው ሁኔታ ሸነሸነው: ለማሌሊት ማጠናከሪያ 55% ለቀይ ሠራዊት 40% እና ለሕዝብ እርዳታ 5% ክፍፍል እንዲደረግ ተወሰነ። በዚሁ አመዳደብ ለሕዝብ ብለው ያስቀመጡት 5% ቢሆን ለማንም አልተሰጠም።*

ይሉናል አቶ ገብረመድህን አርአያ።

አቶ አረጋዊ በርሀም ስለዚህ በጀት ድልድል አውስተው "ከዚያች ቀን ጀምሮ እነዚህ ሰዎች አውሬዎች እንጂ ሰው ሆኖው ሊታዩኝ አልቻለም" ብለዋል።

**የአቶ ገብረመድህን አርአያ ጽሁፍ ይቀጥላል ....**

*ሌላው አሰቃቂ ድራማ የተከሰተው ደጀና እንደገባን በሰር ቦብ ጎልዶፍ የሚመራ ባንድ ኤይድ ተብሎ የሚጠራ የኪነት ቡደን ለሰዩም መስፍን ደብዳቤ በመላክ በድርቅ ለተጎዱት የእርዳታ ገንዘብ ለመስጠት እንደሚፈልጉና በህወሓት በኩል ተረክቦ ለማከፋፈል እንዲቻል ግኑኝነት የሚደረግበትን ሁኔታ የሚገልጽ ደብዳቤ ደረሰው። ... ስብሃት ነጋ ወደ ሱዳን ሄደ ቀጥሎ መለስ ዜናዊ ተነስቶ ወደ ሱዳን ተጓዘ ..... ከባንክ ኤይድ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ፈርመው ከተቀበሉ በኋላ ገንዘቡን በግል የባንክ አካውንት ለሁለት ተካፍለው አስቀምጠው ባዶ እጃቸውን ተመለሱ።*

በእንዲህ ዓይነት አገላለጽና በሚያፈልግበት ቦታ ሁሉ ዋቢ እየጠሩ ነው አቶ ገብረመድህን አርአያ የወያኔን እኩይ ሥራ ያጋለጡት።

"በድርቅ ከተጎዳው ሕዝብ በተዘረፈ ንብረት ወያኔ (ህውሓት ማሌሊት) ፍጹም ሃብታምና ባለፀጋ ለመሆን በቃ" የሚለው የአቶ ገብረመድህን ዓረፍተ ነገር የወያኔን "ከየት ወደ የት" ይገልፃል ብለን እናምናለን። ወያኔ ከረሃብተኛ በመንጠቅ ያደገ፤ የጎረመሰና የገረጀፈ የወንበዴ ድርጅት ነው።

ይህ ነው የወያኔ እውነተኛ ታሪክ። ቆምኩለት የሚለው ሕዝብ ሲራብ የሚፈነጥዝ፤ የእርዳታ እህልን እየነጠቀ የከበረ "ነፃ አውጪ"። በእርዳታ ገንዘብ ጉና የንግድ ድርጅትን አቋቁሞ፤ ኤፈርትንና ደጀናን አደራጅቶ በስታሊናዊው ማሌሊት መሪነት ካፒታሊዝምን እንደሚገነባልን ቃል እየገባለን ያለው ወያኔ ይህ ነው።

በዘመነ ወያኔ ከችጋር ተላቀን ባናውቅም አሁን ደግሞ የባሰ ችጋር እየመጣ ነው። ወያኔ በረሃ ሆኖ ላላዘነለት ሕዝብ ቤተመንግሥት ውስጥ ሆኖ ያዝንለታል ማለት ዘበት ነው። ችጋርና ወያኔ ባንድ ወቅት የተወለዱና እርስ በርስ እየተመጋገቡ የፋፉ መንትያ ችግሮቻችን ናቸው። አብረውም መጥፋት ይኖርባቸዋል።

እየመጣ ያለውን የችጋር አደጋ ለማቋቋም ሁላችንም የተቻለንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፤ ይህ ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊ ተግባር ነው። ከዚህ ጎን ለጎን የሕዝባችን መራብ የወያኔ ሲሳይ እንዳይሆን ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል። ችጋርንና ወያኔን ማስወገድ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነውና ቆርጠን በጋራ እንነሳ!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

[1] አቶ ገብረመድህን አርአያ፣ አቶ አስገደ ገ/ስላሴ እና አቶ አረጋዊ በርሀ በሰሩት ጥፋት በመፀፀታቸው፤ በራሳቸው ተነሳሽነት ሃቅን በመናገራቸው እና ከሁሉም በላይ ደግሞ የበደሉትን ሕዝብ ለመካስ በየግላቸው ባመኑበት መንገድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ በመሆናቸው እናደንቃቸዋለን። ሌሎች ከወያኔ መስመር ወጥተናል የሚሉ በተመሳሳይ መንገዶች የሕዝብ ወገንተኝነታቸውን እንዲያረጋገጡ በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ እንጠይቃለን።

ማስታወቂ

የግንቦት 7 ድምጽ የአድማጮቹን አስተያየት በስልክ ጭምር ለመቀበል እንዲያስችለው አንድ የስልክ መስመር ከፍቶአል ። ስለዚህ ስለፕሮግራማችን አስተያየት ሲኖራችሁ በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661 ልትደውሉልን የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## መራብ የማይገባው ሕዝብ ሲራብ

**ክፍል 2 ፤ የመጨረሻ ክፍል**

የተባበሩት መንግስታት አካል የሆነው የምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ) ጥቅምት 6 ቀን ለተከበረው የአለም የምግብ ቀን መታሰቢያ ባወጣው ዘገባ መሠረት ደህና ዘመን ወይም ወቅት በሚባልበት አመት 35 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ከሚገባው በታች እንደሚመገቡና በዚህም የተነሳ የአካል መቀጨጭ፤የሰውነት መክሳት የህዝቡ ቋሚ ምልክት እንደሆነ ዘግቧል:: አስከትሎም በቂ ምግብ አለማግኘት በአእምሮ ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያሳድር፤ ጉልበት ሥራ ለመስራትም ቢሆን በቂ አቅም በማጣትም የገበሬው ምርታማነት አነስተኛ መሆኑን አስረድቶ አፋጣኝ የመጠንና የአመጋገብ ሥርዓት ለውጥ ካልታየ ትልቅ ችግር እንደሚያጋጥም አስታውቋል:: በመቀጠልም ከ 3 አመት በፊት የጀመረው ድርቅ አድማሱን አስፍቶ ምርትና ሕይወትን እያጨናገፈ እንዳለ፤ ከሞት የሚተርፈው አቅመቢስና ጠውላጋ የሚሆነው ሕዝብ በትንሹ ወደ 50ና 60 ሚሊዮን እንደሚያንስ ስጋቱን ገለጧል::

የእንግሊዝ የአለም አቀፍ ልማት ተራድኦ ሚኒሲቴር ባለፈው ሳምንት ለፓርላማ ባቀረቡት ዘገባ መሰረት ኢትዮጵያ እጅግ ትልቅ አደጋ እንደ ተጋረጠባት፤ ካሁኑ አስቸኳይ እርዳታ ካላገኙ ብዙ ህዝብ ሊያልቅ እንደሚችልና በቅርቡ አገራቸው ለዚህ ጉዳይ ብቻ የሚውል የ19 ሚሊዮን ፓውንድ (380 ሚሊዮን ብር) ችሮታ በተጨማሪ 30 ሚሊዮን ፓውንድ (600 ሚሊዮን ብር) መስጠትዋን ገልፀዋል::

የአሜሪካን የእርዳታ ድርጅት ለኢትዮጵያ ድርቅ መቋቋሚያ እርዳታውን ከፍ እንደሚያደርግና አምናም ካሰበው የበለጠ እርዳታ ለመስጠት እንደተገደደ ዘግቧል::

### ሠ) ምን ይደረግ

በዚህ አስከፊና አስፈሪ ወቅት፣ ወገናችን እንደቅጠል በሚረግፍበት የመከራ ዘመን፣ ይህ ይደረግ ብሎ መወሰን ቀላል አይሆንም:: ችግራችን ብዙ ትግላችንም ባለብዙ ዘርፍ መሆኑ ነው ለውሳኔ እስቸጋሪ የሚያደርገው:: የግንቦት7 ንቅናቄ አመራርና አባላት አሃዙ ከላይ በተጠቀሰው ደረጃ የገዘፈውን ለረሃብና ለአደጋ የተጋለጠውን ህዝብ መከራና ስቃይ በመስማትና በማየት ተረብሸዋል:: በእንዲህ አይነቱ አስከፊ የመከራ ዘመን ንቅናቄያችን እንደወትሮው የፖለቲካ ስራውን እየሰራ ለዚህ ሁሉ የህዝቡ እልቂት ተጠያቂው መለስ ዜናዊና እኩይ ባልደረቦቹ ናቸው ብሎ ብቻ ማለፍ አይችልም:: የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ እስከሚወገድ ህዝባችን በችግር መጠበሱ አይቀርም ብለን ትከሻችንን ሰቅስቀን ልናልፈው የማንችል መርገም ነው በህዝብ ላይ እየወረደ ያለው:: በመሆኑን ግንቦት 7 ንቅናቄ የሃገራችንን አሳዛኝ ሁኔታ ከመረመረ በኋላ የሚቀጥለውን የከፉ ቀን የተግባር ጥሪ ለሁሉም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አስተላልፏል::

1. የውጭ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

   * መለስ ዜናዊና የዘርፊያ አጋሮቹ በሙስና የተጨማለቁ፣ ከዚህም ቀደም ከተራብ ህዝብ ጉሮሮ በመንጠቅ ኪሳቸውን ማደለብ የለመዱ መሆናቸውን በማስረዳት የሚሠጡት እርዳታ በቀጥታ ለተራበውና ለተቸገረው ህዝብ እንዲደርስ እንዲያደርጉ፣
   * የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የእርዳታ እህልን የፖለቲካ ጭቆና መሳሪያ ማድርግ የለመደ መሆኑ እንዲያስታውሱ፤ ለአገዛዙም በቀጥታ የእህል ሆነ የገንዘብ እርዳታ በመስጠት ህዝብ አስከዛሬ ሲደርስበት ከቆየው የሙብት ረገጣና አድሎ በላይ ሌላ ተጨማሪ የጭቆናና የስቃይ ቀንበር ተሸካሚ እንዳያደርጉት፤
   * ድርቅ በኢትዮጵያ በተከሰተ ቁጥር የህዝቡን ስቃይና ሰቆቃ በመገናኛ ብዙኃኖቻቸው እያሳዩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ድረሱለት የሚል የጥድፊያ ጥሪ እንደሚስተላልፉ ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለድርቅ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች ሆነ፣ ድርቅን ተከትሎ የሚመጣን ረሃብ በራሱ መመከት እንዳይችል ዋናው ምክንያት መብቱና ነጻነቱ ተከብሮ፣ የፈጠራና የተነሳሽነት ችሎታውን ተጠቅሞ በገዛ ሀገሩ መስራትና መኖር አለማቻሉ መሆኑን ተረድተው፣ ይህ ህዝብ ለመልካም አስተዳደር ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር የሚደርገውን ትግል እንዲደግፉ ተማጽኖአቸውን እንዲያደርጉ እንጠይቃለን ::

2. ለኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ

   * የገዛ «መንግስቱ» ለጥንብ አንሳ ቀለብነት የተወውን ህዝብ ለመታደግ የአለም አቀፍ ማህበረሰቡና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍ፣ ማመስገንና በተጠናከረ መንገድ እንዲቀጥሉበት መጠየቅ እና እርዳታቸው በወያኔ እንዳነጠቅ እንዲጠነቀቁ ማሳሰብ፤ እና
   * በረሃብ መሞትን ከሃገራችን ለዘለቄታው ማጥፋት የሚቻለው የዜጎች ነጻነት ሲረጋገጥ በመሆኑ ለጊዜዓዊው ብቻ ሳይሆን ለዘላቂ መፍትሄ በጋራ እንድነሳ እንጠይቃለን።

3. ለኢትዮጵያ ህዝብ

   * ሁሌም ክፉ ቀን በመጣ ቁጥር ካለችህ አነስተኛ ጥሪት ለባሰበት አካፍለህ ወገንህን እንደምትታደግ እናውቃለን:: እየመጣብን ያው ክፉ ቀን እንደተንባዮቹ ከሆነ ከመቼውም የከፋ ነው:: አሁንም እንደልማድህ የተራበን ወገንህን፣ አንዱ ካንዱ ሳትለይ፣ የዘመኑ ዘረኞች የዘሩትን የከፋፍለህ ግዛ ዘረኛ መርዝ አምክነህ ሁሉንም ችግረኛ ታደግ::
   * ያለህበት የሰቆቃና የሲቃ ህይወት ለአንዴና ለሁሌም እንዲያከትም ለዘመናት የተሸከምከውን ምኞትክን ማሳካት የምትችለው ግን ራስክን የሃገርህ፣ የሃብትህና የመብትህ ጌታ ማድርግ የሚችል ስርአት ስትመሰርት መሆኑን አትዘንጋ:: በአናትህ ላይ ለሰፈሩት ዘራፊ ዘረኞች «የተራብ ወገኔ እረዳለሁ:: እናንተ ግን በረሃብ ቅስሜን ሰብራችሁ የዘላለም ባሪያ እንድታደርጉኝ አልፈቅድላችሁም» በላቸው::

4. አለም ዙሪያ ተበትኖ ከሃገሩ ውጭ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ

   * ችጋርና ጠኔ የአባት የእናትህን የእህትቶችና የወንድሞችህን በር እያንኳኳ ነው:: የድረሱልኝ ጥሪቸያው ጥለሃቸው ከተሰደድክባቸው መንደሮችና ቀየዎች እየተንደረደ በቴሌቪዥንህ መስኮት በጣረሞት ምስላቸው ተደግፎ ቀርቦልሃል:: ወገናቸው ያልሆነው ሌላው አለም ሲንጫጫ አንተ ዝም ብለህ ልታያቸው የምትችልብት አንጀት እንደሌለህ እናውቃለን:: እርዳታህን በቀጥታ ለተቸገረው በሚያደርሱ ድርጅቶችና ቡድኖች አማካይንት ለግስ:: ሌሎችንም አቅሙ ያላቸውን የቅርብና የሩቅ ዘመዶችህንና ወገኖችህንም አስተባብረህ እርዳታ አሰባስብ::
   * ይህ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደህዝብ በአለም ላይ የውረደትና የሃፍረት መለያችን የሆነው ረሃብ እንዴት ለአንዴና ለሁሉ ግዜም መቆም እንደሚችል አስብ:: በምትኖርባቸው የበለጸጉ ሃገሮች እንደሌላው ቦታ ሁሉ ድርቅ ያጋጥማል:: ዝናብ ይጠፋል:: ትላልቅ ወንዞች ትናንሽ ምንጮች እስኪሆኑ ይመነምናሉ:: በድርቅ የተነሳ ግን እንኳን በሚሊዮኖች አንድም ሰው አይሞትም:: ለምን ብለህ ጠይቅ:: ይህ ድል የተገኘው ፈሪሃ ህዝብ የሚሰማው መንግስት በሃገር ላይ ከማቆም፣ ከመልካም አስተዳደርና ከዜጎች መብቶች መከበር ጋር ተያይዞ መምጣቱን ልብ በል:: የሃገራችንና የህዝባችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ከውርደት እንድንገላገል፣ እኛም ዛሬ በሃገራችን ስልጣን ላይ ባሉት ዘረኛ አምባገነን ዘራፊዎች ምትክ ፈሪሃ-ህዝብ የሚገዛቸው ባለሰልጣናትን ህዝብ የሚሠይምበትን የፖለቲካ ስርዓት መፍጠር እንደሚኖርብን ተረዳ:: ይህ ችግር ከስሩ እንዲነቀል የህዝባችንን የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል በያለህበት ባለህ አቅም ሁሉ ደግፍ::

የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላት በሙሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የዚህን አስከፊ የቸነፈር ዘመን እልቂትና ጥፋት ለማሳነስ የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ አይቦዝኑም:: በዚህ ቀውጢ ጊዜ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመታደግ ደፋ ቀና ከሚሉ ማናቸውም አካላት ጋር በመተባበር ይሰራሉ::

ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትም ተመሳሳይ እርምጃ ይወስዳሉ ብለን እንጠብቃለን:: ከእዚህ በተጨማሪ ግን ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ልብ ሊሉት የሚገባ ነጥብ አለ:: ከአመት አመት እየከፋ ብዙ ህዝብ የሚቀስፈው ረሃብ ዛሬ ያልገባበት የሃገራችን ክፍል የለም:: የሙብት እረገጣውና አፈናውን ዘርና ጎሳ ሳይለይ በሁሉም የሃገሪቱ ህዝብ ላይ እንደተጫነ ሁሉ ረሃብም ዛሬ ወትሮው ከሚታወቅበት የሃገራችን ሰሜናዊ ክልል ወጥቶ ምስራቁንም ደቡብና ምእራቡን አዳርሷል::

ግንቦት 7 ከዚህ በላይ የኢትዮጵያን ህዝብና የኢትዮጵያን የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሊያስተባብረ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ አለ ብሎ አያምንም:: መተባበርና የኢትዮጵያ ህዝብን መታደግ የሚገባን ትናንት ነበር፤ አርፍደናል:: ሁላችንም በዚህ ረሃብ በአንድ በኩል ፈጣሪን በሌላ በኩል የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ እንደምንጠይቅ ሁሉ እኛስ ሃገርንና ወገን ላስቀደሙ ራእዮች ራሳችንን ተገዥ አድርገን ለህዝባችን በግዜ ባለመድረሳችን ተጠያቂዎች አንሆንም? ነፍስና ህሊናችንን በሚገባ ዳሰን ይህን ጥያቄ በሚገባ መመለስ ይኖርብናል:: ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው ሃቀኛ ምላሽ፣ የሁላችንንም ህሊና ኮርኩሮ የወገኖቻችንን የመከራ ቀን ለማሳጠር ሁላችንም ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን በአንድነት ረሃብን ለማጥፋት፣ ነጻነትን ለመቀዳጀት፣ መብታችንን ለማስከበር እንድንነሳ እንደሚያደርግን ተስፋ አለን::

**ውድቀት በረሀብተኛ ህዝብ ስም ለሚነግዱት እፍረተቢስ ዘረኞች!!!**

**ትብብር የኢትዮጵያን ህዝብ የመከራ ዘመናት ለማሳጠር!!!**

**ግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ !!!**

## የመለስ በህክምና ወደ በልጅዬም . . . ከገጽ 1 የዞረ

እየሻከረ የመጣው የግንቦት 7 ድምጽ በመለስ ዜናዊ ጤና ዙሪያ የሚያወጣው ትክክለኛ መረጃ አምባሳደሩን እንቅልፍ እየነሳው ከመጣ በሁዋላ እንደሆነ አስረድታለች።

የአምባሳደር ተብየው ብርሀኔ ገ/ክርስቶስ የግል ባህሪ እጅግ አሳፋሪና አንድ አገርን ወክሎ ከተቀመጠ ባለስልጣን የማይጠበቅ መሆኑን የምትናገረው ወ/ት ገነት፣ በሴት ልጆች ላይ የሚያደርሰው ግፍ ተነግሮ የማያለቅ መሆኑንም ገልጻለች።

መለስ ዜናዊ ለህክምና ወደ ብራሰልስ መመላለሱን ታውቅ እንደሆን ላቀረብንላት ጥያቄ ወ/ት ገነት በሰጠችው መለስ " መለስ ዜናዊ ለረጅም ጊዜ ወደ ብራሰልስ እየመጣ ህክምና ያገኝ እንደነበር ገልጻ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የጤናው ሁኔታ እየከፋ በመምጣቱ በተደጋጋሚ እንደሚመላለስ ተናግራለች።" አምባገነኑ መለስ ለህክምና ሲመጣ የሚያርፈው በአምባሳደሩ ቤት መሆኑን የምትገልጸው ገነት፣ ከእርሱ ጤና ጋር የሚስማማ ምግብ ትሰራ የነበረው እራሷ እንደነበረች ተናግራለች። መለስ የእርሱዋን ሽሮ ወጥ በእጅጉ ይወደው እንደነበር በሳቅ በታጀበ ገለጻ የምትናገረው ገነት፣ በቅርቡ ወደ ብራሰለስ በመጣበት ጊዜ ይመገብ የነበረው ደረቅ ምግቦችን ሳይሆን የዶሮ ሾርባ ብቻ እንደነበር አስረድታለች። አንቺ ያዘጋጀሽውን ምግብ አምኖ ይመገብ ነበር ወይ ተብላ ለተጠየቀችው ደግሞ " እኔ ምግቡን ልስራው እንጅ በምግቡ ውስጥ የምጨምራቸውን ነገሮች ቆመው የሚከታተሉ ሰዎች አሉ። እነሱ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው የማደረገውን ሁሉ በአንክሮ ይከታተላሉ። በመጨረሻም ምግቡን በቅድሚያ ይቀምሱና ትንሽ የቆያሉ። ከዚያ በሁዋላ ነው ምግብ የሚቀርብለት" ብላለች። መለስ ዜናዊ ምግብ ሲቀርብለት ከብርሀነ ገብረክርስቶስ በስተቀር ሌላ ሰው አብሮት እንደማይቀመጥ የምትናገረው ወ/ት ገነት፣ የአምባሳደሩ ባለቤት አብራ ከመለስዜናዊ ጋር ስትመገብ አለማየቷን ተናግራለች። ብርሀኔ ገብረክርስቶስ አሜሪካን አገር በነበረበት ወቅት ከባለቤቱ ጋር በነበረበት አለመጣጣም ለፊች ፍርድቤት ቀርቦ በባንክ ሂሳቡ ውስጥ የነበረ አርባ ሚሊዮን ዶላር እንዲካፈል ጥያቄ አንደቀረበበት እና ገንዘቡ ለአለቃው ለመለስ ዜናዊ በአደራ የተቀመጠ መሆኑን መናገሩ በወቅቱ በሰፊው ተዘግቦ አንደነበር አይዘነጋም። በ ወ/ት ገነት ምስክርነት ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ከቀድሞ ባለቤቱ ጋር ከመታረቁ በፊት ሚሚ ስብሃቱ ከተባለቺው የቀድሞ ቪኦኤ ባልደረባና የአሁኑ የኢፍቲን ዋና አዘጋጅ ጋር በተደጋጋሚ ብራስልስ ላይ እየተገናኙ አብረው የአውሮጳን መዝናኛ ስፍራዎች ያስሱ እንደነበርም አጋልጣለች።

የግንቦት 7 ድምጽ የአምባገነኑንና ዘረኛውን መለስ ዜናዊ የጤንነት ሁኔታ እየተከታተለ መዘገብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ መለሰ ጤነኛ መስሎ ለመታየት የማያደርገው ጥረት እንደሌለ ምንጮቻችን የገለጹ ሲሆን፣ ወደ ብራሰልስ መምጣቱና መሄዱ እንደተዘገበ ወዲያውኑ ወደ ናይጀሪያ በማምራት ጤነኛ መስሎ ለመታየት ሞክሯል። ሰሞኑን ደግሞ ከእነ እንጂነር ሀይሉ ሻውል ጋር ጎን ለጎን ተቀምጦ ጤነኛ መስሎ ለመታየት ቢጥርም፣ ሁኔታውን ቀረብ ብለው የተመለከቱ ዘጋቢዎቻችን እንደገለጹት ከሆነ ግን ሰውየው ፊቱ ገርጥቶ፣ ንግግር ለማድረግ ጉልበት አጥሮት ቃሎችን እየተንተባተበ ሲደጋግም ተስተውሏል።

## አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በተመሳሳይ HUNETA የወያኔ እመቃ ከደረሰባቸው በርካታ የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ አባል መካከል የፓርቲውን መሪ ብርቱኳን ሚደቅሳን መታሰር ለመቃወም ከሚዘጋጀው ቃሌ ከተሰኘ ፕሮግራም ሲመለስ መስከረም አምስት ቀን የታሰረ አባል እንደሚጠቀስ አዲስ አድማስ ዘግቧል።የምእራብ ጎጃም ነዋሪ የሆነው የአንድነት አባል ቃሌ የተሰኘውን ዝግጅት ከተካፈለ በሓላ ወደ ቤቱ ሲሄድ መታሰሩን በስብሰባው ላይ ተናግሮአል።የአንድነቱ አባል ከመታሰሩም በላይ በራሱ እና በባለቤቱ ላይ ድብደባ መፈጸሙን መስክሯል።

ሀያ የሚሆኑ የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ አባላት የምስክርነት ቃላቸውን በስብሰባው ለተገኙ እንግዶች ያካፈሉ ሲሆን ስማችን ከተገለጸ ወያኔ እንደገና ሌላ ግፍ ይፈጽምብናል ብለው ስለሰጉ ስማቸው እንዳይገለጽ ጋዜጠኞችን መማጸናቸውን የአዲስ አድማስ በዘገባው አስፍሯል። በአድሲ አድማስ ሪፖርት መሰረት በስብሰባው የተለያዩ የምእራብ ሀገራት ዲፕሎማቶች መገኘታቸውም ታውቋል።

የወያኔ የግፍ ሰለባ የሆኑት የአንድነት አባላት የምስክርነት ቃል ከሰአት በሓላም ቀጥሎ እንደነበረ የገለጸው አዲስ አድማስ በተመሳሳይ ቀን አስር ሰአት ላይ ፓርቲው በወያኔ ወህኒ በግፍ የምትማቅቅበትን መሪውን እስር ተቋውሞ የሚያደርገው ቃሌ የስነጽሁፍ ምሽት ለአስረኛ ጊዜ መደረጉን ዘግቧል።የአንድነት ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱኳን ሚደቅሳን እስከአሁን የፓርቲ አባላት ፤የትግል ባልደረቦችዋ እና ዘመድ አዝማድ እንዲጠይቋት እንዳልተፈቀደ ተገልጿል። አንድነት በአባላቶቹና ደጋፊዎቹ ላይ የተፈጸመውን ሰቆቃ የምስክርነት ቃል በሚያሰማበት ወቅት የወያኔ ቁንጮ የሆነው ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ የዜና ሽፋን እየተሰጠው የሚገኘውን የምርጫ ስነምግባር መመሪያ ተብዬ ሰነድ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ 3 ፓርቲዎች ጋር ሲፈራረም አንደነበር ይታወሳል ።

## የወያኔ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በቅርቡ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወ/ት ሙኒ የተባለች የአዲስ አባበ ነዋሪ በበኩሏ በግንቦቱ ምርጫ ወቅት የቅንጅት ቀንደኛ ደጋፊ እንደነበረች ተናግራ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፖለቲካ የሚባል ነገር መስማት እንደማትፈልግ ይሁን እንጅ ለወ/ት ብርቱካን መፈታት አጥብቃ እንደምትጸልይ ተናግራለች።

የአድማስ ኮሌጅ ተማሪ የሆነ ወጣት ሲናገር ደግሞ "አንድን ህዝብ አንድ ጊዜ ማታለል ይቻላል፣ ሁለት ሶስት ጊዜ ግን ማታለል አይቻልም፤ እንዲህ የሚያስቡ እራሳቸው ሞኞች መሆን አለባቸው። እኛ እኮ አንድ ጊዜ በወያኔ ተታለናል። ሁለተኛ ከተታለልን ችግር ያለው እኛ ጋ ነው ማለት ነው" ሲል ተናግሯል። በፓርቲዎች መካከል ተደረገ የተባለው ስምምነት አስደስቶት እንደሆን ሲጠየቅም "ስምምነትን ማን ይጠላል፣ የጠላነው ስምምነቱን ሳይሆን ተስማሚዎችን ነው" ብሏል።

ሪፖርተራችን የተለያዩ መረጃዎችን አሰባስቦ እንደገለጸው ምርጫውን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ያለው የህዝቡ ስሜት እጅግ ቀዝቃዛ መሆኑን ተናግሮ፣ ህዝቡ ከምርጫው ይልቅ ትኩረቱ ረሀቡ፣ ድህነቱ፣ የኑሮ ውድነቱና የመብት አፈናው ላይ መሆኑን ተናግሯል።

በተያያዘ ዜናም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መጪውን የይስሙላ ምርጫ አስመልክቶ መግለጫዎችን በማውጣት ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ፣ "በወያኔ የምርጫ ቧልት አለመሳተፍ የዜግነት ግዴታ ነው" በሚል ርእስ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ "ውጤቱ አስቀድሞ በሚታወቅ ምርጫ ዜጎች በምርጫው መሳተፍ እንደሌለባቸው ገልጿል። "የደም ዘር የያዘው ስርአት ህዝቡን ፈጅቶና የህዝብን ድምጽ ሰርቆ በጉልበቱ በስልጣን መቀጠሉን ዜጎች ሁሉ የታዘቡት ምጸት ነውና ዛሬ የህዝብ መሰረታዊ ጥያቄዎች ቅንጣት ታህል ምላሽ ሳያገኙ አረመኔው ስርአት በአሸናፊነት በሚወጣበት ምርጫ መግባቱ ለአገርም ለህዝብም የሚጠቅም እርምጃ አይደለም" የሚለው የኢህአፓ መግለጫ፣ ምርጫ የተባለውን ሂደት በተመለከተ መሰረታዊው ችግር የስነ-ስርአትና የስነ ምግባር ሳይሆን ሀገሪቷ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስር መሆኑዋና ለነጻ ምርጫ ምንም እድል አለመኖሩ ነው ሲል አትቷል።

ኢህአፓ በመግለጫው፡ የህዝብ ድምጽ መሰረቁን፣ ከ200 ያላነሱ ዜጎች መገደላቸውንና ገዳዮች እስከ ዛሬ ለፍርድ አለመቅረባቸውን፣ ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች አለመፈታታቸውን፣ የምርጫው ህግ አለመቀየሩን፣ ወታደሩና ፖሊሱ በአንድ ቡድን ቁጥጥር ስር መሆኑንና ዜጎች ያለፍላጎታቸው የወያኔ አባላት ካልሆናችሁ እየተባሉ መገደዳቸውን በማስረጃነት በመጥቀስ፡ መጪው ምርጫ የወያኔ ፍላጎት ማርኪያ ብቻ እንደሚሆን ከገለጸ ቦኋላ ህዝቡ ለወሳኙ ህዝባዊ አመጽና ሁለገብ ትግል እንዲዘጋጅ በመፍትሄነት ጥሪ አቅርቧል።

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ . . . ከገጽ 1 የዞረ

እኔ አቅመ ደካማና ችግረኛ ነኝ። ተስፋዎቼ ልጆቼ ነበሩ። ተስፋየ ሁሉ ከልጆቼ ጋር አብሮ ሄዷል። እኔ ከእንግዲህ ወደ ልጆቼ እሄዳለሁ እንጅ ልጆቼ ወደ እኔ አይመጡም። የማዝነው ልጆቼ የተሰዋንለት አላማ ምን ደረሰ ብለው ሲጠይቁኝ የምሰጣቸው መልስ ምንም የሚል መሆኑ ነው" ሲሉ በሀዘን ተናግረዋል።

መለስ ዜናዊ በሰጠው ትእዛዝ ከ200 በላይ የሚሆኑ መገደላቸው፣ ወደ አንድ ሺ የሚጠጉ መቁሰላቸውና በአስር ሺዎች የሚጠጉ ወደ እሰርቤት መወርወራቸው የሚታወስ ነው።

## አንድ ኢትዮጵያዊ በአገሪቱ እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት በመቃወም በቤተ መንግሰት ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ

ሳምሶን ጌታቸው የተባለው የአዲስ አባበ ነዋሪ ሰሞኑን ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ የገለጸልን ሲሆን፣ ወደ አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ ቢሮ በማምራት ብቻውን መፈክሮችንና አቤቱታዎችን ሲያሰማ ቢውልም ወጥቶ የተቀበለው ሰው እንዳልነበረ ታውቋል።

አቶ ሳምሶን የዋጋ ግሽበትን ፣ የነዳጅ ዋጋ መጨመርንና የኑሮ ውድነቱን በማስመለከት አቤቱታዎችን ሲያሰማ እንደነበር የገለጸው ሪፖርተራችን፣ ከቤተመንግሰት በመቀጠል ወደ ነዳጅ ድርጅቶች በመሄድ በቅርቡ የተደረገውን የነዳጅ ጭማሪ ተቃውሟል። አቶ ሳምሶን ያቀረበው አቤቱታ እንዲህ የሚል ይዘት እንዳለው ዘጋቢያችን ገልጿል" በእድሜየ ተሳስቼ ባውቅም አሁን ለምገፋው ኑሮ የሚያበቃ ብዙ ግፍ ግን የሰራሁ ነኝ ብየ አላስብም። ታዲያ ምን ይሆን ጥፋቴ? ከአገሬ በምንም መልኩ መሰደድ እና ያላገር እንደተወለደ በሰው አገር ተሳቆ መኖር አልፈልግም። ግን ደግሞ አገሬ ውስጥ አሁን ባለው ሁኔታ በፍጹም መኖር አልቻልኩም። እጅግ ተቸግሬያለሁ ኑሮ ከብዶኛል"። ወጣት ሳምሶን ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ የተመለከቱ በርካታ ወጣቶች ጥሪ አቅርቦላቸው ቢሆን ኖሮ አብረነው እነሰለፍ ነበር ማለታቸውን ለአንድ ሬዲዮ በሰጠው ቃለ መጠይቅ መግለጹ ተዘግቦአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661